EthioLion

# ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ

አፍሪካ አገራችን በተፈጥሮ ሀብት እጅግ የታደለች ፣ በደንና ዱር አራዊት የተዋበች ፣ በከርሰ ምድር ማዕድናት የበለጸገች መሆኗ ይታወቃል ፤ ታዲያ ይህንን አስጎምጂ ሀብቷን ያዩና ለመዝረፍ የቋመጡ ምዕራባውያን ከአውሮፓ ገስግሰው አፍሪካን እንደ ቅርጫ ተጣጥለው ለብዙ ዘመናት ሀብቷን ሲቦጠቡጡና ሲመዘብሩ ቆይተዋል ፣ እንዲሁም ህዝቧን በአሰቃቂ ሁኔታ ለሰቆቃና ለመከራ ዳርገውት እንደነበር የቅርብ ጊዜ ክፉ ትዝታ ነው ። በዚህ ጭካኔና አረመናዊነት በተሞላበት አገዛዝ የሰዎችን ደም እንደጎርፍ ማፍሰሳቸው ንብረታቸውን ያለገደብ መዝረፋቸው ለመላው አፍሪካዊ ህዝብ ዛሬም ያልሻረ የመከራ ትውስታ ሆኖ ቁጭትና ንዴቱ አሁንም እንደ እናት ሞት ከውስጡ አልወጣለትም ።

ምዕራባውያን ቅኝ ገዢዎች በአፍሪካ ውስጥ የሚገኘውን ሀብት በዓይን ከሚታየው በእጅ ከሚዳሰሰው ባሻገር በከርሰ ምድርም ያለውን ወርቁን ፣ አልማዙን ፣ መዳቡንና እንዲሁም በርካት የሆኑ የተፈጥሮ ማእድናትን ቀን ከሌት በሩጫና በትጋት  ጠያቂና ከልካይ በሌለበት ለዘመናት ሲመዘብሩና ሲበዘብዙ ፣ አገሪቷን ሲያራቁቱ መቆየታቸው ሚስጥርም አልነበረም ። እነሱም ባለፈው ተግባራቸውም ዛሬም ቢሆን ይኮሩበታል እንጂ አላፈሩበትም ። በተመዘበረው ሀብትና ነጻ አፍሪካዊ ጉልበት አገራቸውን ገነቡበት ፣ ህዝባቸውን አበለጸጉበት ።

ዛሬም በሺዎች የሚቆጠር ማይል ተጉዘው በደቡብ አፍሪካ ላይ የሰፈሩትና አገራቸው ያልሆነውን አገራቸው ያደረጉት መጤዎች የኢኮኖሚና የፖለቲካውን አውታር ተቆጣጥረው ባለሀብትና ባለንብረት የሆኑት የቀድሞ አፓርታይድ አራማጆች አፍሪካን እንዴት ያለ ክፉ ገጠመኝ ደርሶባት እንደነበር የሚያመለክት አይነተኛ ምሳሌ ነው ።

አሁንም ቢሆን በአውስትራሊያ በአቡርጂኒስ ጥቁር ሕዝብ ላይ እየተካሄደ ያለው እጅግ የከፋ እንደሆነ ይታወቃል ። የሰው ልጅ ተወልዶ ባደገበት እትብቱ በተቀበረበት ለብዙ ሺህ ዘመናት የትውልድ ሀረጉን በሚቆጥርበት ምድር ላይ መምጫው ያልታወቀ በድንገት እንደ ደራሽ ውሃ ገስግሶ በቦታው የሰፈረው መጤ ኃይል የጥቁሮችን መሬትና ሀብት ቀምቶ እሱ ባለ ሀብትና ባለ ሀገር ሲሆን ባለ ሀገሩና ባለ ሀብቱ ግን አገሩንና ክብሩን ተቀምቶ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ወይንም ባነሰ ሁኔታ እየታየ ዛሬም በባዕዳን ንብረቱና ሀብቱ እየተመዘበረ ከእንሰሳ ባነሰ ሁኔታ የጭንቅና የሰቆቃ ኑሮን እንዲገፋ የጭካኔ ብይን ተበይኖበት የግፍ አተላ እንደጋፈ አንድ ቀን ሳያልፍለት ህይወቱ ከዚህ ዓለም ታልፋለች ። በምትኩም ልጆቹና የልጅ ልጆቹ

EthioLion

ወላጆቻቸው በተንዙበት የፍዳ ህይወት ተተክተው ህይወታቸው ካሉት በታች ከሞቱት በላይ ሆና የተለመደውን የመከራ አዙሪት ዞራ ይሄም ህይወት ፣ ኑሮ ተብሎ ይህችን የጭንቅ ዓለም በማይቀረው ሞት ይሰናበቷታል ።

ወራሪ ኃይል አፍሪካን በተቀራመተበት ወቅት የሰው ልጅ በሚሊዮኖች በሚቆጠር እንደ ቅጠል የረገፈበት ፤ ደም እንደ ጎርፍ የፈሰሰበት ፤ ጥቁር ሕዝብ እንደ ከብት ጥርሱ እየተገለፈጠ ፣ ክብደቱ እየተመዘነ ፣ ጡንቻው እየተሞከረ የተሸጠበት ፣ የጭካኔ በትር የዘነበበት ፣ ግፍና በደል የቆጠረበት ጊዜ እንደነበር ታሪክ መዝግቦ ይዞታል ።

ታዲያ የሰው ልጅ ቀንበር ሲጠናበትና በደል አላቆም ሲል ይዋል ይደር እንጂ ለአመፅ መነሳሳቱ አይቀሬ ነው ፤ ስለሆነም ይህ ህዝብ ጭቆናውን መቋቋም ሲሳነው መሳሪያውን አንስቶ እምቢኝ አልገዛም ብሎ በየቦታው ዱር ቤቴ ብሎ አመፁን ተያያዘው ፤ ለህገሩና ለነጻነቱ መሰዋቱንና መዋደቁን በተግባር ማስመዝገብ ጀመረ ፤ በትዕቢትና በማናለብኝነት የተወጠሩትም ቅኝ ገዢዎች የትግሉን መራራነትና ቁርጠኝነት መገንዘብ የግድ ሆነባቸው ፤ ቀድሞ እነሱ አዳኝ ፣ ጥቁሩ ታዳኝ ፣ እንዳልነበሩ ሁሉ ዘመን ተለውጦ በተራቸው እነሱም መታደን ፤ መገደል ፤ ስለመጣባቸው ለወደፊትም ተሸንፎና ተዋርዶ መውጣቱ የማይቀርላቸው መሆኑን ሲገነዘቡ ይህንን አስጎምጂ ሀብትና ንብረት ለባለቤቱ በሰላም አስረክበው መውጣ አልመረጡም ፤ ይልቁንም ያ የማይጠግበው ሆዳቸው አሁንም በአፍሪካ ህዝብ ሀብት ካልተደጎመ እንደማይሆንላቸው ስለሚያውቁት ህዝቡን በዘዴ ከፋፍለውና ለወደፊት ከባድ ችግርና አለመግባባት ሰፍኖ እርስ በርሱ እየተጨፋጨፈ እንዲኖር ለማድረግ ህዝቡን በጎሳ ፤ በሀይማኖትና በመሳሰሉት የመከፋፈል ስራቸውን በሰፊው ተያያዙት ፤ ከዚህም መሰሪ ተግባራቸው አንዱና ዋነኛው ባሉበት ሀገር ሁሉ ካሉት ብሄረሰቦች አንዱን በመቅረብና በማባበል ፣ እነሱ ከሌሎች ወንድሞቻቸው በብዙ ሁኔታዎች የተሻሉና የበለጡ እንደሆኑ በመስበክ ፤ ይህ ዘዴ የማይሰራ ከሆነ ደግሞ ሌሎች ወንድሞቻቸው እንደሚንቋቸውና ፤ እንደሚጨቁኗቸው ፤ በፖለቲካው ፤ በማህበራዊ ኑሮ ፤ በስነልቦናና እምነትን በመሳሰሉት ሁሉ በወንድሞቻቸው እንደሚበደሉ ወይንም ዝቅ አድርገው እንደሚያዩዋቸው በመስበክና ያልነበረውን እንዳለ አድርጎ በማሳመን የነሱ ወገንና የነሱ ተቆርቋሪ መስለው በመቅረብ በፈጠራና የልብ ወለድ የጥላቻ መርዝ አስክረውና አሳምነው ከወንድሞቻቸው ይልቅ ወራሪውን ተቀብለውና አምነው እሱን አጋር አድርገው በገዛ ወንድሞቻቸው ላይ ለመዝመት ታጥቀው እንዲነሱ የሚገፋፉ መርዛቸውን ነዙ ። ይህንንም ስውር ደባቸውን እውን ለማድረግ እንዲያስችላቸው የትምህርቱንም ሆነ የኢኮኖሚውን አውታር አብዛኛውን ዜጋ በመንፈግ ለሰበካቸው ሰለባ ለሆነው ጎሳ ብቻ ዘመናዊ ትምህርት በመጠኑም ቢሆን እንዲሰጥ በማድረግ ወጥመዳቸው ውስጥ አስገቧቸው ፣ በኢኮኖሚውም ረገድ እንዲሁ ከቀሩት ወንድሞቻቸው የተሻለ ሁኔታ እንዲደርሱ በማድረግ አገሪቷን ሳይወዱ በግድ ተገፍተው ሲወጡም እነዚህ ወጥመድ ውስጥ የገቡት የብሄረሰብ ቡድኖች ቀድሞ

EthioLion

በተደረገላቸው ምድሎ የተነሳ ከሌሎች ወንድሞቻቸው የተሻለ ቀለም ስለቆጠሩና በቅኝ ግዛቱም ወቅት አንዳንድ የኢኮኖሚ አውታሮች ውስጥ ገብተው እንዲያድጉ ስለተደረገ በነጻነታቸው ወቅት በቀላሉ ስልጣኑን የመጨበጥ ሰፊ እድል ገጠማቸው ።

ቅኝ ገዢዎች አገሪቱን በሚገዙበት ወቅት አንተ ከወንድምህ ትሻላለህ በሁሉም ነገር ትበልጣለህ ወይም በሌሎች ወንድሞችህ ትናቃለህ ፣ ትበደላለህና የመሳሰሉትን ስለተሰበኩ እነሱም ያንን የተሰበኩትን እውነት ነው ብለው አምነው ስለተቀበሉ ከሌሎች ወንድሞቻቸው የተሻሉ መሆናቸውን ለማሳየት ወይንም ተጨቁነን ነበር በሚለው የተገሩም ከሆነ አሁን በተራቸው ይጨቁኑን ነበር የሚሏቸውን ክፍሎች እነሱ የበላይ መሆናቸውን ለማሳየት በሚደረግ ግብግብ በሁለት ወንድማማቾች መካከል አለመግባባትን እየተፈጠረ ስለመጣ ይኸው አፍሪካ ቀደም ብሎ በተሸረበላት ወጥመድ ውስጥ ቀስ በቀስ እያዘገመች ሄዳ ዛሬ የትርምስና የጦርነት አውድማ ሆና እናያለን ። ይህ ቅንብር የቀድሞ ቅኝ ገዢዎች በድጋሚ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ተመልሰው ወደ አፍሪካ የምዝበራ ስራቸው እንዲሰማሩ የተመቻቸ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል ። የተፈለገውም የሩቅ እቅድና አላማቸው ይህው ነበርና ዛሬ ተሳክቶላቸው የዘራቸውን ፍሬ መልቀም ጀምረዋል ።

ይህ በጎሳ ፣ በቋንቋ ፣ በሀይማኖትና በመሳሰሉት የመከፋፈል ተንኮል በቅኝ በተገዙ አፍሪካውያን አገሮች ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በቅኝ ባልተገዛነውም በኛ ላይ ተመሳሳይ ተንኮል ተፈጽሟል ። የጥንስሱም ውጤት ዛሬ ዐይኑን አፍጥጦ ፣ ጥርሱን አግጥጦ ፣ አለመግባባትና ግጭት እየፈጠረ እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም ። ፋሽስት ኢጣሊያ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አገራችንን በወረረችበት ወቅት ይህንን የመከፋፈል ተግባር በሰፊው ስትሰራበት እንደቆየች ይታወቃል ፤ ይህንን የፋሽስቶች ሴራን አሜን ብሎ በመቀበልና በማራገብ ዛሬ ተምረናል ፣ አውቀናል የሚሉ ባዶና ተመጻዳቂ ጠባብ ብሄርተኞች በጸረ ኢትዮጵያዊነት ሽንጣቸውን ገትረው ሲሟገቱና አገራችንን ለማፈራረስ ቀን ተሌት ተግተው ሲሰሩ እያየን ነው ። እነኚህ ጠባብ ብሄርተኞች ዛሬ መጽሀፍ ቅዱሳችን ብለው የሚያነበንቡትና ለማመሳከሪያም የሚጠቅሱት ይህንኑ ፋሽስት ኢጣልያ ያበረከተላቸውን ተረት ተረት ነው ።

በስልጣን ላይ ያለው የወያኔው ጠባብ አገዛዝም የዚሁ ውልድ እንደሆነ የማይካድ ሀቅ ነው ። እምነቱና ሥራው ሁሉ ያንን ያመነና የተቀበለ ፣ እሱንም ተግባራዊ ለማድረግ ደፋ ቀና የሚል ፤ የምዕራባውያን ወራሪዎች ጥቅም አስጠባቂና ሎሌ በመሆን የኢጣሊያ ፋሽስቶች ያስረከቡትን የአጥርና የክልል እንቶ ፈንቶ በተግባር ለማዋል ይሄ ያንተ ክልል ፤ ይሄኛው የኔ ክልል ፤ ይሄ የኔ ሰንደቅ ዓላማ ፤ ይሄኛው ደግሞ ያንተ ሰንደቅ አላማ ፤ እያለ ፈጣሪዎቹ ነጮችንና አረቦችን ለማስደሰት ፣ እናት ሀገሩን ለመግደልና ለመቀበር ምን ልታዘዝ እያለ እጥፍ ዘርጋ ሲልና ሲማፀን ይታያል ።

EthioLion.com

EthioLion

ምዕራባውያኑ እንደዚህ ያሉ ጠባቦችንና ሆድ አደሮችን ስልጣን ላይ ማውጣትና ትናንሽ መንደር መሰል አገሮችን መመስረት ለብዝበዛቸው አመቺ መሆኑን ያውቁታል ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ይህንን መሰል የጥፋት ጎዳና አፍሪካውያን እንዲያራምዱ ከፍተኛ ድጋፍ ያደርጋሉ ። በአብዛኛው የአፍሪካ አገሮች ውስጥ በስልጣን ላይ የሚገኙ አምባገነኖችም በምዕራባውያን ተኮትኩተውና ታንፀው የተሰሩ ፣ የአንድ ፋብሪካ ምርቶች ለመሆናቸው ምንም ማመሳከሪያ አያሻም ። ስለሆነም እነዚህም የተንኮል ምርቶች ለስልጣን ላበቋቸው ፈጣሪዎቻቸው በምላሹ በያሉበት አገር ሁሉ ቅራኔን በማስፋፋት ፣ አገሪቷን ለባዕድ ምዝበራ ማመቻቸት ፣ የሚጠየቁት ዋጋ ነው ፤ ስለሆነም ዛሬ በነዚህ ሆድ አደሮች የተነሳ አፍሪካ ቀድሞ ወደነበረችበት የጨለማ ዘመን እንድታመራ አምባገነኖች የታሪካዊ ጠላቶቿ ተባባሪ ሆነው አገር ሲያፈራርሱና ሲበትኑ ለማየት ተገደናል ።

ይህ ከብዙ በጥቂቱ ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን ለቀው ከመውጣታቸው በፊት የተጠቀሙበት ዘዴያቸው ነው ። አፍሪካን ለብዙ መቶ አመታት እንደ ክፉ ጥላ ወጊ ሲከታተላት የሚኖር በርካታ ችግሮችንም ተክለውባት ነው የሄዱት ። ለምሳሌም አፍሪካ ውስጥ የሚገኙ አገሮችን የድንበር ክልል ሲያሰምሩ ሆን ብለው ለወደፊት በጎረቤት አገሮች መካከል ግጭትን የሚቀሰቅስ ፣ ጦርነትን የሚጋብዝ ተንኮል የተላበሰ ምስቅልቅሉ የወጣ ድንበር አስምረው መውጣታቸው ከወጥመዳቸው አንዱ ክፍል ነው ። ይህ ሁኔታም ዛሬ በሀገራችን ኢትዮጵያና ቀድሞ በእንግሊዝ የቅኝ አገዛዝ ስር በነበረችው ጎረቤት አገር ሱዳን መካከል መምጫው በማይታወቅ እንግሊዛዊ የጦር መኮንን ተሰመረ የሚባለው ድንበርና የቀድሞ እናት አባቶቻችን የሚያውቁትና ጠብቀውት ያቆዩልን ድንበር ባለመጣጣሙ በሁለቱ ጎረቤት አገሮች መካከል ትልቅ ውዝግብ ሆኗል ። ወደፊትም ይህ ሁኔታ በቀላል የሚፈታ እንዳልሆነ መተንበይ ይቻላል ። ይህ በምዕራብ ኢትዮጵያ ብቻ ተወስኖ የቀረ ችግር ሳይሆን በምስራቁም ተመሳሳይ ችግር ያስከተለና ተደጋጋሚ ጦርነቶችንም የጫረ ነው ። ለወደፊትም ቢሆን በሁለቱም አቅጣጫ ከፍተኛ ችግሮች ሊገጥመን እንደሚችል አያጠያይቅም ።

የውጪ ኃይል ጣልቃ ገብነትና ተንኮል በድንበር ብቻ ተወስኖ የቀረ ሳይሆን በተፈጥሮ ሀብትም ላይ ተመሳሳይ ችግር እንዲነሳ ከፍተኛ ሴራ ተፈጽሟል ፣ አሁንም በምሳሌነት አገራችን ኢትዮጵያ የገጠማትን መግለጹ ጥሩ ማስረጃ ይሆናል ፤ የአባይ ወንዝ አንጡራ ሀብት የኢትዮጵያ እንደሆነ ለማንም የተሰወረ አይደለም ፤ ሆኖም ግን ይህንን የደለበ ሀብታችንን በተመለከተ ሙሉ የባለቤትነት መብት ቀርቶ በድርሻ ይገባናል ብለን እንዳንጠይቅ እንኳን በነጮች ተንኮልና ሴራ ጉረሮአችንን ተይዘን ለዘመናት የአባይ ወንዝ ለሀገራችን አንዳችም አገልግሎት ሳይሰጥ የባእዳን ሲሳይ ሆኖ ቆይቷል ። በቅርቡም በአባይ ተፋሰስ በሚገኙ አገሮች መካከል የተነሳው የይገባኛልና ጥያቄና ባለመብትነት ያስነሳው ውዝግብ የነዚሁ የታሪካዊ ጠላቶቻችን የቀደመ ተንኮልና ሴራ ውጤት ነው ። የአባይ ወንዝ ባለሀብት የሆነችውን ኢትዮጵያን ሳይጨምር በግብጽና በቀድሞ ቅኝ ገዢዋ በነበረችው በእንግሊዝ መንግስት መካከል በተደረገ የተንኮል

EthioLion

ስምምነት የተነሳ ዛሬ የአባይ ውሀ ተጠቃሚ በሆኑ አገሮች መካከል ከፍተኛ የሆነ አለመግባባትን ፈጥሯል ። በተለይ በሀገራችን ኢትዮጵያና በግብጽ ፤ እንዲሁም በኢትዮጵያና ፤ በሱዳን መካከል አለመግባባትና መቃቃርን እየፈጠረ ነው ። ለወደፊትም ይህ የውሃ ባለሀብትነትና የይገባኛል ጥያቄ ከምን ሊያደርሰን እንደሚችል ለመተንበይ ነብይነትን አይጠይቅም ።

ዛሬ ጠላቶቻችን የተጠነሰሰልን ስውር አገዛዝ ከወትሮው በአይነቱ እጅግ የተለየና የረቀቀ ነው ። ስለሆነም ጠላት እንደ ከዚህ ቀደሙ ጦራቸውን ሰብቀው ፤ ባህር አቋርጠው ፤ ለዘረፋና ለግድያ የሚገሰግሱ ሳይሆኑ ፤ አቀራረባቸውና አመጣጣቸው እጅግ በተወሳሰበ ዘዴ ስለሆነ አፍሪካውያን እውነተኛ ጠላታቸውን ለመለየት እንኳን ተስኗቸው እርስ በርስ ሲናከሱ እነሱ ከዳር ቆመው ያላግጡበታል ።

አዲሱ ስልታዊ አመጣጣቸው አንድን አገር በቀጥታና ግልጽ በሆነ መንገድ በወረራ ቅኝ ለመያዝ ሳይሆን በርካታ የምዕራባውያን አገሮች ሆነው ከጥቁር ሕዝብ በስተጀርባ በሸረቡት ደባ ልማትና በጎ አድራጎትን ተንተርሰው አንዱ የምዕራብ አገር የሚሰራውን ሌላኛው ሳያጋልጥና ሳይጋፋ ሁሉም የየግል ጥቅማቸውንና ፍላጎታቸውን እያሟሉ ለጋራ ጥቅም አፍሪካን ማወክና ማራበሽ ፤ አፍሪካውያንን በብሄር ከፋፍሎ እርስ በርሱ እንዲጋጩ ማድረግ ፤ የሀይማኖት ግጭቶች እንዲፈጠሩ መሸረብ ፤ ሁሉንም የብሄርም ሆነ የሃይማኖት ተቋሞች ከኋላ ቆሞ አለሁልህ በርታ ማለትና የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ እርዳታ በመስጠት አይሎ የተገኘውን ጎሳም ሆነ የሃይማኖት ክፍል ወደ ስልጣን እንዲመጣ ማድረግና የነሱን ጥቅም እስካስጠበቀ ድረስ ያልተቆጠበ እርዳታና ድጋፍ አለመንፈግ ናቸው ።

ስልጣን ላይ ያወጡትም ቡድን እንዳይከዳቸው ለመጠባበቂያና ለማስፈራሪያ የሚሆን በስልጣን ላይ ካለው የተለዩ የብሄረሰብ ክፍሎችን ወይንም የሃይማኖት ቡድኖችን በስውር ማደራጀትና ለነሱም አስፈላጊውን እርዳታና ትብብር መስጠት ፣ ይህ አሰራር ስልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ ጠላት አለኝ ብሎ እንዲሰጋ ስለሚያደርገው ፍፁም የነሱ ታዛዥና ጥገኛ እንዲሆን ይረዳል ። ሌላ ተቀናቃኝ መፈልፈልና ማደራጀት ለማስፈራሪያነቱ ብቻ ሳይሆን ለረጅም ዘመን የብዝበዛ መረብም ለመዘርጋት የተመረጠ ዘዴ ነው ። ይህም ማለት " *ሁለት ባላ ትክል አንዱ ቢሰበር ባንዱ ተንጠልጠል*" ይሆናል ። አሁንም ለዚህ ሰውር ደባቸው ከምስኪን ኢትዮጵያችን በተሻለ በምሳሌነት የሚጠቀስ አገር አይኖርም ።

ምእራባውያን ጥንትም ሆነ ዛሬ ከአፍሪካ የሚፈልጉት የደለበና የማይነጥፍ ሀብቷን ፣ የልጆቿን ነጻ ጉልበት እንጂ ለአፍሪካውያን መብትና ነፃነት ምንም አይነት በጎ ምኞት እንደሌላቸው ሳይታለም የተፈታ ነው ። ስለሆነም ይህንን የንዋይ ጥማቸውን ለማርካት ዛሬ እነሱ ዘመቻ መውጣት እንደማይኖርባቸው ጠንቅቀው አውቀውታል ። ይልቁንም "*ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ*" በሚል መርህ ካለፈው በበለጠ እራሳቸውንም አደጋ ላይ ሳይጥሉ ፣ እነሱም በወራሪነት ፣ በግፈኝነት ሳይወነጀሉ ስራውን በሆድ አደርና አገር በቀሎች በማሰራት

EthioLion

ተመሳሳይ ውጤት ማግኘት እንደሚቻል ከምን ጊዜውም በላይ እየተረዱት መጥተዋል ፣ በተግባርም እያዋሉት ይታያል ።

ይህንን ስውር ምኞታቸውንና አላማቸውን እውን ለማድረግ በስልጣን ላይ ቢቻል ከአንድ ብሄር ፣ ወይንም ጎሳ ካልሆነም አንድ አይነት የሆነ የሀይማኖት እምነት ካላቸው ብቻ የተውጣጣ ቢሆን ይመርጣሉ ። ይህ ሲሆን ስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ በቀላሉ ከቀረው ህዝብ ጋር ስለሚቃቃርና ቅራኔ ውስጥ ስለሚገባ ተቀዳሚ ምርጫቸው ነው ። ስልጣን ላይ ያለውንም አገዛዝ ማናቸውንም ከህዝብ ጋር ቅራኔ ውስጥ ሊያስገባው የሚችለውን ነገር ሁሉ እንዲፈጽም በስውር ያበረታታሉ ፤ ባደባባይ ግን ለይስሙላ ይኮንናሉ ። ይህ እንዲፈጠር የሚሹት ዋነኛው ምክንያት በሀገሪቱ ውስጥ አለመረጋጋትና መመሰቃቀል እንዲኖር ነው ፤ ይህ ሁኔታ ሲፈጠር ደግሞ ስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ይደነግጣል ፣ ይፈራል ፣ ስልጣኑ ላይ እንዳለ ለመቆየት የሚረዳው እረዳት ይሻል ። ያኔ እነሱ እኛ ከጎንህ አለን በማለት እጃቸውን ይዘረጋሉ ፣ አገዛዙም የማይበገር አጋር አለኝ ብሎ በትዕቢት ይወጠራል ፣ ሕዝብ ይንቃል ፣ ፈጣሪዎቹ ያዘዙትን ሁሉ ይፈጽማል ፣ በነሱም ተመክቶ ካለልክ ሕዝብን ይበድላል ፣ ያሰቃያል ፣ እነሱም ያንን ስለሚገነዘቡ ወጥመዳቸው ውስጥ እስከተደፈቀ ድረስ በማናቸውም ሁኔታ ሁሉ በስውርም ይሁን ባደባባይ አብረውት በመቆም ጸረ ሕዝብነታቸውን በድጋሚ ያረጋግጣሉ ፣ ዘረፋውም አለተቀናቃኝ በሰፊው ይቀጥላል ።

ምዕራባውያንም በተፈጥሯቸው ንዋይን እንጂ ማንንም ስለማያምኑ ከሁሉም በላይ የግል ጥቅማቸውን ስለሚያስቀድሙ በሰው ልጆች ላይ ለሚደርስ ሰቆቃ ቁብም አይሰጣቸው ። ወዳጅ ብለው የያዙትንም እንደ ወያኔ ያለውን ደካማና አናሳ ቡድን እንኳን ከነሱ ጉያ እንዳይወጣ ለማድረግ ሌላ የሚደነግጥበትና የሚበረግግበት በነዚሁ ምዕራባውያን የተቀፈቀፈ ጠላት አደራጅተውለታል ። ለዚህም የኦሮሞው "ኦነግና" የሱማሌው "ኦብነግ" አይነተኛ ምሳሌዎች ናቸው ። እነዚህ ወያኔን ለማሸበር ዘወትር ጠላት እንዳለው ሊወድቅ እንደሚችል ለማስፈራሪያ የተፈጠሩ ወያኔ ወዳጆቼ የሚላቸው የምዕራባውያን ቅፍቅፎች ናቸው ። ወያኔውንም ሆነ ተገንጣዩ የሚረዱት በነዚሁ ሰው በሎች እንደሆነ ለማንም ያልተሰወረ ያደባባይ ሚስጥር ነው ። እንግዲህ የጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ዘዴና ብልሀት ከሞላ ጎደል ይህንን ይመስላል ።

በሀገራችንም ሆነ በመላው አፍሪካ እየተፈጠረ ያለው የጎሳም ይሁን የሀይማኖት አለመግባባትና ውዝግቦች በሁለት ወንድማማቾች መካከል ቀድሞ ያልነበረና ለብዙ ሺህ አመታት ተከባብረውና ተፋቅረው እንዳልኖሩ ሁሉ አሁን በምዕራባውያን ጣልቃ ገብነትና በነሱ ሴራ አጠንጣኝነት አንዱ ባንዱ ላይ እንዲነሳ ፣ አንዱ ሌላውን እንደበደለ አርጎ በማናፈስ ፤ ያልነበረ ታሪክ በመፃፍ ውዝግብ እንዲፈጠር እያደረጉ ለግጭቱም እነሱው ዱላ አቀባይ በመሆን ፣ ነገሮችን በማጋጋልና በማራገብ ሁኔታዎችን በረጅም ጊዜ ጥናት

አመቻችተው ስለመጡ ቀድሞ ያመለጣቸውን የዘረፋ መረብ ዛሬ በሰፊው ዘርግተው ሁሉን ተግባራዊ ለማድረግ በቅተዋል ።

ይህንን መሰልና እና ከዚህም በላይ የሆነ በቂ ማስረጃ እያለ ታዲያ ፣ ዛሬም በአንድ ኢትዮጵያና በአንድነት እናምናለን ፤ የጎሳና የሀይማኖት ልዩነትንና እንዲሁም በጎሳና በሀይማኖት ለፖለቲካ ስልጣን የሚደራጁትን እናወግዛለን የሚሉት ቡድኖች እንኳን ሳይቀሩ ወያኔን የፈጠሩና ኮትኩተው ፣ አሳድገው ፣ አስታጥቀው ፣ ዛሬ ለደረሰበት ደረጃ ያበቁትን ደጀኖቹንና አንደ እንግሊዙ ቶኒ ብሌር ፣ ከዚያም ጎልደን ብራውን ፣ የዛሬው ደግሞ ዴቪድ ካሜሮን ፤ እንደ አሜሪካው ጆርጅ ቡሽ ፣ ዛሬ ባራክ ኦባማ ፤ የነዚሁ ምዕራባውያን የመበዝበዣ መዋቅር የሆነውን የተባበሩት መንግስታትና የአውሮፓ ሕብረትን ከወያኔ ሰቆቃ እንዲያወጧቸው በየደጃፋ እየተንከራተቱ ሲማጸኑ ማየት *"ለቀባሪው ማርዳት"* ይመስላል ። ባገራችን የሚፈጸመው ግፍና በደል ሁሉ እነሱ ሳያውቁትና የነሱም ስውር ድጋፍ ሳይኖርበት አንዳችም ነገር አይፈጸምምና ፤ መለሰ ዜናዊ ወይንም መንግስቱ ኃይለማርያም ዘንድ ሄዶ እነሱው ለገደላ ያሰማሯቸውን ካድሬዎች በነመልስ ወይንም መንግስቱ ትዕዛዝ የማይንቀሳቀሱ ይመስል በካድሬዎች የሚደርስብንን በደልና ፍጅት አይታችሁ ፍትህን ስጡን ብሎ ወደነዚህ አምባገነኖች እንደመጉረፍ ይመሰላል ። አሁንም ባገራችንንና በህዝቧ ላይ የሚደርሰውን በደል ምዕራባውያኑ የማያውቁት ከነሱ ትዕዛዝ ውጪ የተሰራ ነገር ያለ ይመስል ወደነሱ አማልዱን ፣ አድኑን ፣ እያሉ መማፀን ውሃ መውቀጥ ይሆናል ።

በዕውነት ይህንን ከማንም ያልተሰወረና ያልተደበቀን ሃቅ እንዴት ማየት ተሳነን? ጠላታችን ወይንም ጠላቶቻችን እነማን እንደሆኑ እውን ማወቅ አንቆቅልሽ ሆኖ ይሆን? በስልጣን ላይ ያለው ወያኔስ የጠላቶቻችን እረጅም እጅ ወይንም ነገረ ፈጅ መሆኑን እናውቃለን? መልሱን ላንባቢያን ።

ድል ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ !

ብሄርተኝነትና ጠባብነት ይከስማሉ !

አይምሮ ዳኛቸው

EthioLion.com